**To - Radio Vaticana**

**Prog. Etio/Eritreo**

**00120 Citta del Vaticano**

**Fax. 00390669883844**

**Email: amartig@vatiradio.va**

መጋቢት 12, 2003

## *በጃፓን በደረሰው የተፈጥሮ አደጋ የኢትዮጵያ የሀይማኖት መሪዎች የሀዘን መግለጫ አስተላለፉ*

መጋቢት 2 2003 ዓ.ም ጃፓንን በመታው ከፍተኛ የመሬት መንቀጥቀጥና የሱናሜ አደጋ ለተጎዱና ህይወታቸውን ላጡ የሀገሪቱ ዜጎች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ፓትርያርክ ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ፣ የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ሼህ አህመዲን ሼህ አብዲላሂ፣ የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ ብጹዕ አቡነ ብርሃነየሱስ ሱራፌል፣ የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ ፕሬዚዳንት ዶክተር ዋቅስዩም ኢዶሳ በጃፓን ኤምባሲ በመገኘት የተሰማቸውን ጥልቅ ሀዘን ገልፀዋል፡፡

ጠንካራ፣ የሥራ ሰውና ሰላም ወዳድ በሆነው በጃፓን ህዝብ ላይ በደረሰው በዚህ አሳዛኝ አደጋ የሀይማኖት መሪዎቹ ባስተላለፉት የሀዘን መግለጫ መልዕክት ጃፓን በዓለም ካሉት ሦስት ጠንካራ ኢኮኖሚ ካላቸው ሀገራት የምትመደብ በመሆኗ በመልካም ግንኙነት በማደግ ላይ ላሉ ሀገራት ኢትዮጵያንም ጨምሮ እያደረገች ያለችውን ድጋፍ ጠቅሰዋል፡፡ በተለያዩ ጊዜያት በአለም ላይ በደረሱ ተፈጥሮዊም ሆነ ሰው ሰራሽ አደጋዎች የጃፓን ህዝብና መንግስት አፋጣኝ መፍትሄና ድጋፍ በመስጠት የሚታወቅ መሆኑንም አክለው ገልጸዋል፡፡

የሃይማኖት መሪዎቹ በመልዕክታቸው በጃፓን ህዝብ ላይ በደረሰው አደጋና ችግር እግዚአብሔር እንዲረዳቸውና እንዲጠብቃቸው በፀሎት ከጎናቸው እንደሚቆሙና ሰላም ወዳድ የሆኑት ጃፓናውያንም በደረሰባቸው ችግር ተስፋ ባለመቁረጥ ሁሉ ለሚቻለው ፈጣሪ አምላክ ካሉበት አስቸጋሪ ሁኔታ እንዲያወጣቸው መፀለይ እንደሚገባቸው ጠቁመዋል፡፡

የኢትዮጵያ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ጠቅላይ ጽ/ቤት

ማህበራዊና ህዝብ ግንኙነት ማስተባበሪያ